# የቋንቋ እርዳታ አገልግሎቶች

RTD ዋጋውን ለመገምገም ስርአት አቀፍ የዋጋ ጥናት እና ፍትሃዊነት ትንተና እያካሄደ ነው።  የእርስዎ ተሳትፎ እና አስተያየት ተቀባይነት አላቸው። የቋንቋ እርዳታ አገልግሎቶች ያለ ምንም ክፍያ ይሰጣሉ። መሳተፍ ከፈለጉ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎን ኢሜል ያድርጉ farestudy@rtd-denver.com ወይም ይደውሉ 303.299.6000. እንደአማራጭ ደግሞ የበይነመረብ አሳሽዎን ከእንግሊዝኛ እርስዎ ወደመረጡት ቋንቋ ለመቀየር ከዚህ በታች ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ።  ከዚያ ወደታሪፍ ጥናት ድረ-ገጽ ይመለሱ rtd-denver.com/farestudy ለፕሮጀክት ማሻሻያዎች እና ለመሳተፍ.

## የበይነመረብ አሳሽዎን ቋንቋ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል


Google Chrome ........................................ 1
Mozilla Firefox ........................................ 3
Microsoft Edge ........................................ 5
Apple Safari ........................................ 8


### Google Chrome

1. የGoogle Chrome አሳሽን ይክፈቱ።
2. በመስኮቱ ላይኛው ቀኝ ጠርዝ ላይ ያለውን  አዶውን ጠቅ ያድርጉ።
3. ከሚታየው ተቆልቋይ ምናሌ ውስጥ **Settings** ይምረጡ።
4. በቀጣዩ መስኮት፣ 

ተቆልቋዩን ጠቅ ያድርጉ።
5. በ *ቋንቋዎች* ክፍል ላይ ጠቅ ያድርጉ።
6. በ *ቋንቋዎች* ክፍል ውስጥ፣ በ **ቋንቋ** አማራጩ በቀኝ በኩል ያለውን *ተቆልቋይ* ጠቅ ያድርጉ።



7. በሚታየው ምናሌ ውስጥ Add languages ማስፈንጠሪያውን ጠቅ ያድርጉ።

8. በቀጣዩ ማያ ገፅ፣ ከአንድ ወይም ከዛ በላይ ቋንቋ(ዎች) (A) ቀጥሎ ያለውን አመልካች ሳጥኑን ጠቅ ያድርጉ እና በመቀጠል **Add** የሚለውን አዝራር (B) ጠቅ ያድርጉ።




9. የእርስዎ አዲስ የተመረጡ ቋንቋዎች በቋንቋ ምናሌ ውስጥ መታየት አለባቸው። አንዱን ለመምረጥ፣ ከቋንቋው በስተቀኝ ያለውን ⋮ አዶ ጠቅ ያድርጉ እና **Display Google Chrome in this language** ከሚለው ቀጥሎ ባለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።




10. አዲሱን ቋንቋ ለማሳየት **Relaunch** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ ወይም የChrome አሳሽዎን ይዝጉና እንደገና ይክፈቱ።

# Mozilla Firefox

1. የMozilla Firefox አሳሽን ይክፈቱ።

2. በአሳሹ መስኮቱ ላይኛው ግራ ጠርዝ ላይ ያለውን  አዶ ጠቅ ያድርጉ።

3. ከሚታየው ተቆልቋይ ምናሌ ውስጥ **Settings** ይምረጡ።
4. በቋንቋ ክፍል ስር፣ 

አዝራሩን ጠቅ ያድርጉ።




5. በመስኮቱ ውስጥ፣ **Select a language to add** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።



6. የሚፈልጉትን ቋንቋ (A) ጠቅ ያድርጉ፣ **Add** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ እና ከዚያ **OK** የሚለውን አዝራር (B) ጠቅ ያድርጉ።




7. አዲሱን ቋንቋ ለማሳየት አሳሽዎን እንደገና ያስጀምሩ።

# Microsoft Edge

1. የMicrosoft Edge አሳሹን ይክፈቱ።
2. በአሳሹ መስኮቱ ላይኛው-ቀኝ ጠርዝ ላይ ያሉትን **Settings and more icon** ጠቅ ያድርጉ።
3. በተቆልቋይ ምናሌ ውስጥ፣ ከታች አጠገብ **Settings**።



4. በማያ ገፁ በግራ በኩል፣ በቅንብሮች ስር፣ **Languages** ጠቅ ያድርጉ።



5. በቋንቋዎች ክፍል ስር፣ **Add languages** የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ።




6. በሚታየው ጥያቄ ውስጥ አሳሹ እንዲያሳይ የሚፈልጉትን ቋንቋ(ዎች) ይምረጡ እና ከዚያ **Add** የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ።




7. ወደ ቋንቋዎች ክፍል ተመለሰው፣ የመረጡትን ቋንቋ ያግኙ እና በቀኝ በኩል ያለውን ⋯ አዶ ጠቅ ያድርጉ። ከዚያም፣ **Display Microsoft Edge in this language**።
8. የ Restart አዝራሩን ጠቅ ያድርጉ ወይም አሳሹን ዘግተው እንደገና ይክፈቱ።

# Apple Safari

Safari በ macOS ውስጥ ተዋህዷል። በመሆኑም፣ በSafari ውስጥ የሚታየውን ቋንቋ ለመቀየር ወደ Mac ቋንቋ ቅንበሮችዎ መግባት አለብዎት።

1. በማያ ገፁ በላይኛው-ግራ ጠርዝ ላይ የApple ምናሌ ለመክፈት እና **System Preferences** ለመምረጥ የApple አዶን ጠቅ ያድርጉ።




2. **Language & Region** መስኮት ውስጥ ቋንቋ እና ክልል የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።



3. በቋንቋ እና ክልል ምናሌ ውስጥ **Preferred languages**፣ ከታች ያለውን **+ ምልክት** ጠቅ ያድርጉ።




4. በተቆልቋይ ምናሌው ውስጥ ቋንቋን ይምረጡና ከዚያ **Add** የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ።



5. ወደ አዲሱ ቋንቋ እንዲቀይሩ ሊጠየቁ ይገባል። ያ ካልሆነ፣ አዲሱን ቋንቋ በቀዳሚው ማያ ገፅ ላይ ወደ ምናሌው አናት ላይ ጠቅ ያድርጉት-እና-ይጎትቱት (በደረጃ 3 ላይ የሚታየው)።




6. አዲሱ የቋንቋ ቅንብሮች እንዲተገበሩ **Restart Now** የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ።

